# የዕሥራ ምዕቱ አባቶች ለሣልሳይ ሺሕ ዓመት ልጆች

ነት መከራ እየተቀበሉ አሁን ላለንበት ለዕሥራ ምዕቱ ፍጻሜም አደረሱን። ታዲያ አሁን ያሉት የዕሥራ ምዕት አባቶችስ ምን አስረክበውን ያልፉ ይሆን? የሣልሳይ ሺሕ ዓመት ልጆች ጥያቄ ነው።

በዕሥራ ምዕቱ ዋዜማ የተፈጠረው መለ ያየት እንዳለ ወደ ሣልሳይ ሺሕ ዓመት ይሻ ገር ይሆን? ከዚህ ጋር ሊታለፍ የማይገባው ጠባብ አስተሳሰብስ? የዚያ የመሐመድን ወገኖች የተቀበለው የኢትዮጵያዊው የንጉሥ አርማህ ልጆች የራሳቸው ልጆች፣ መጠጊያ አጥተው የሚባዝኑበት አሠራርስ እንዴት ይፈታ ይሆን? ግልጽ ለማድረግ የቤተ ክስቲያኒቱን ትምህርት ተምረውና አስመስክረው ሁሉም ወደ መሐል ሀገር በመምጣት ብቻ ደጅ የሚጠኑበት ሁኔታ በምን ይስተካከላል? በዚያው ባሉበት እንዲያገለግሉ ምን ታስቦላቸዋል? በከተማ የሚጋፉት በገጠር እንዲያገለግሉ፣ የከተማው ድርጎ ወደ ገጠር ለምን አይወ ጣም? የሚሉ ጥያቄዎችን የሚመልስ አሠራርን ነው የምናስረክበው ወይስ አሁን ያለውን ፍልሰት? ገዳማትንና ገዳማውያንንስ እንደ ጥንቱ ሀገርን የሚፈውሱ ለሀገርና ለሕዝብ ሳይቀር ሕይወታቸውን አሳልፈው የሚሰጡ፣ አቡነ ጴጥሮስን የመሰሉ አባ ቶች የሚፈልቁባቸው ምንጮች ሆነው እና ስረክባቸው ይሆን? ወይስ በአንዳንድ ቦታ ዎች መታየት እንደ ጀመረው ሥራ የጠላ ተቀላቢ መጠራቀሚያ አድርገን? የአብነት ትምህርት ቤቶችንስ እንደሚታሙት እንደ ጥቂቶቹ የሥር ማሽ እና የቅጠል በጣሽ ዋሻዎች ወይስ ትርጓሚውን የሚያቀኑ፣ አብነት የሚያጸኑ ሊቃውንት መፍለቂያዎች አድርገን? ልጆች እየጠየቁ ነው፤ እንዴት ታስተላፉልናላችሁ እያሉ።

ኅብረተሰብ ተኮር ልማትንም ቢሆን ትውልዱ ይጠይቃል። ምርኮኞችን እና ፍሬምናጦስን አሳድገው፣ ልጅ አድርገው፣ ዜግነት ሰጥተው ለጵጵስና ያበቁት የእነዚያ ስመ ጥር አባቶች ልጆች የሆኑት የዛሬዎቹ የዕሥራ ምዕት አባቶች ለሣልሳይ ሺሕ ዓመት ልጆች በዚህስ በኩል ምን ያስረክቡ ይሆን? ዛሬ የመንገዱን ዳር የሞሉት ልጆች የእነ ማን ናቸው? የዛሬዪቱ እናት ለልጆቿ የም ታወርሰው ምንድን ነው? ፍቅርንና እንክ ብካቤን ወይስ ጐዳናን? የወለደችው ብቻ ማለት አይደለም። በዙሪያው ያለችው ሁሉ።

በፈረንጆች የፋሽን ሥነ ልቡና ስክሮ በዓል በመጣ ቁጥር ሰፋና መጋረጃ መቀየርን ወይስ ልጆችን እንሥቶ ዓለምን የሚለውጡ አድርጎ ማሳደግን? አንተስ ባለጸጋው አባት ، ምንድን ነው የምታወርሰን? ይላሉ ልጆች። የመኪና ራዎልት መቀየርን ብቻ ነው ወይስ ለጐዳና ሰዎችም አሮጌ ልብስ እንኳ መቀየርን? የቱን ይሆን የሣልሳይ ሺሕ ዓመት ልጆች በርግጥ የእግዚአብሔር ሥጦታዎች ናቸው ወይስ የጎዳና?

ሀገርን በመጠበቅስ ቢሆን ምን እናስረ ክባቸው ይሆን? በርግጥ ኢትዮጵያ የክርስ ቲያን ደሴት እንደ ሆነች ትቀጥል ይሆን? ጥንት ተሰድደው ከመጡት ከ80 ከማይበል ጡት የመሐመድ ወገኖች የቀሩት ጥቂቶች ብቻ ነበሩ። አሁን ግን 32 ሽ ደርሰዋል፣ ከእነርሱ ግን አንዳንዶቹ ሳያፍሩና ሳይ ፈሩ ከግማሽ በላይ ሆነናል የሚሉበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። ይህ ሁሉ የምን ምልክት ይሆን? እነርሱ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ልቦ ለድ ፈጠራዎቻቸውን ያዘንባሉ፣ ከእኛ ወገን ሃይማኖቱ የተሰማው «ስለ እኔ በሰው ፊት የሚመሰክርልኝ ቢኖር...» የሚለው ቃለ ወንጌል ትዝ የሚለው ያለ አይመስልም። ለምን ይሆን?» በርግጥ ለልጆቻችን የምናስረክበው ምንድን ነው? ሃይማኖት? ምግ ባር? ፍቅር? አንድነት? መተማመን? ምን? ቆም ብሎ ማሰብ ሳይጠይቀን ይቀራል? ትላንት ሞቃዲሾ ላይ ቀድሰው፣ ምእመኑን አቁርበው አስረክበውን ነበር።

አሁን ግን በጅማና በአካባቢው ላይም ጥያቄ ተነሣብን፣ ትላንት የመን ላይ ቀድሰን ማቁረብ ብቻ ሳይሆን በዓለም የተደነቁ ቤተ መቅደሶችን ሠርተን ዛሬ አሻራዎቻቸውን እናያለን፣ ዛሬ ግን ይፋትም የእናንተ አልነበረም ሊሉን ጀመሩ። ታዲያ የምናስረክባት ሀገር ታሪኳን አጥፍተን ነው ወይስ እውነቱንም ጭምር ጽፈን ?

የየመኑ እስላም ተጠምቆና ተምሮ ለእጨጌነት መብቃቱን፣ /የእጨጌ ዕንባቆምን ታሪክ/፣ የሸህ ዘከርያን ተጠ ምቆ አባ ዘካርያስ ተብሎ ክርስትናን ማስፋፋቱን ስላልጻፍንላቸው ንጉሥ አርማህ ሰልሞ ሞቷል ሲባሉ ልጆ ቻችን መጠየቅ ጀመሩ። በመንበረ ጽዮን በትግራይ መስጊድ ነበረበትን? ይሉናል። ስለካሌብ ዋሻ ዝም ስላልን ስለፈጠራው ነጃሽ የተጋቱትን እያቀረሹ በታሪክ በሽታ መለከፋቸውን ነገሩን። ታዲያ የዕሥራ ምዕቱ አባቶች የምናስረክበው ሀገራዊ ታሪክ ምንድን ነው? የሣልሳይ ሺሕ ዓመት ልጆች እየጠየቁን ነው። በርግ ጥም መልስ ያስፈልጋቸዋል።

ይህን ሁሉ ያነሣነው ውስጣችን ለዚህ ምን ያህል ተዘጋጅቷል? የሚለውን ለማየት አስፈላጊ በመሆኑም ነው። በዚህ በዕሥራ ምዕቱ ዋዜማ የተፈጠረውን ልዩነት ለመፍ ታት ዛሬ ካልታሰበ መቼ ይታሰባል? ልዩነትን ወደ ሣልሳይ ሺሕ ዓመት ማሻገርስ ለምን ይጠቅማል? የቤተ ክርስቲያኒቱን የሐሳብ፣ የአስተዳደርና የትምህርት መርሐ ግብርስ መቼ ሊነደፍ ይችላል? መጪውን የሉአላዊነት ወይም ዓለም አቀፋዊነት -ግለጸበቷለፀዘቷተፀኔ? ሁኔታ አልፎ ሕዝቡን በክርስትናው ሊያጸና የሚችል መንገድ ተቀይሶ ይሆን? ወይስ እንደ እስካሁኑ ጊዜውን ባላገናዘበ ልማዳዊ መንገድ እንጓዝ ይሆን? የቤተ ክርስቲያኒቱን አንጡራ ሀብት እያነሡ የሚጠቀሙበትንስ አስቁሞ ሙሽራይቱን ቤተ ክርስቲያን ከነዝርግፍ ጌጧ ማስረከቡ የማን ሥራ ይሆን? የሙሽራው ብቻ ሊሆን አይችልም። ሙሽራይቱን የሚያስ ዘርፍ ሚዜ ሊኖር አይችልም። ታዲያ በሐዋርያት የተተኩ ካህናት ሚዜዎች፣ ሙሽራይቱን ካልጠበቁ ሥራቸው ምን ይሆን?

በርግጥ እስከአሁን ብዙ ነገሮች ሳይበረዙ ደርሰውናል። ሃይማኖት ከነምግባሩ፣ ዶግማ ከነቀኖናው፣ ታሪክ ከነትውፊቱ፣ ሥርዓት ከነባሕሉ ደርሰውናል። አባቶች

# የዕሥራ ምዕቱ አባቶች ለሣልሳይ ሺሕ ዓመት ልጆች

በማስረከብ ልጅ ችም በመረከብ ይመሰገናሉ:: የልጆችም ጥያቄ አይጠላም:: ተረድቶ መቀበል የሚገባ ነውና:: መሪው ትውልድም ጠያቂ ስለሚሆን መልሱን ለማወቅ በወጣም ለማስተላለፍ መረዳት አስፈላጊ ነገር ነው:: አባቶችም ለማስረከብ በሚገባው መንገድ መዘጋጀት ያስ ፈልጋቸዋል:: እንኪን ታሪክንና ሀገራዊ ሀብትን ልጅንም ጎጆ ለማውጣት በቂ ዝግጅት ይጠይቃል::

የሣልሳይ ሺሕ ዓመት ልጆችም ዝም ብለው የሚቀበሉ አይመስሉም:: መጀመሪያ የምናስረክባቸውን ሊያውቁት ይፈልጋሉ:: ቀጥለው ለምንና ምኑን እንዴት እንደሚ ቀበሉን መረዳት ይፈልጋሉ:: ከዚህም በላይ ጉድፉን እንሥተን፣ እንጽተን፣ ወልውለንና ሰንግለን እንድናስረክባቸው ይጠይቁናል:: በዚህም ብቻ አያበቁም ከአባቶቻችን የተረከ ብንበትን ደረሰኝ አይተው፣ አሁን ካለው ጋር በማነጻጸር፣ አለመጉደሉን ማረጋገጥ ይፈል ጋሉ:: ከዚህም ጋር ለዚህ ክቡር ሀብትና ጸጋ ማስቀመጫ ይሆን ዘንድ የሠራነውን የዘመ ናችን የአደራ መዝገብ አስቀድመው ማየት ይፈልጋሉ:: በመጨረሻም የቀደሙ አባቶች ያስተላለፉበትንና ያስረከቡበትን ጥበብ ብቻ ሳይሆን፣ እነርሱም ለሚቀጥለው ትውልድ እንዴት ማድረስ እንዳለባቸው የአስተዳደር ሥልታዊ መርሐ ግብር -ስተረቷተጽገፀቸ ፐለቷነ? መጠየቃቸው አይቀሬ ነው:: ስለዚህ መዘጋጀት ይጠበቅብናል፣ የዕሥራ ምዕቱ አባቶች ለሣልሳይ ሺሕ ዓመት ልጆች::

Mahibere Kidusan©2005, All Rights Reserved
አስተያየት ለመስጠት: webmaster@eotc-mkidusan.org